## *የግል ማስታወሻ*
## *ከጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ጋር 33ቱ የኦሮሞ ሽማግሌዎች ያደረግነው ምክክር*

***ቀን: 24/2/2001***

***ቦታ : ቤተመንግሥት***

***ሰዓት: 4:20 ጧት ያበቃበት ሰዓት 6:01***

በመጀመሪያ ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ለኦሮሞ ሽማግሌዎች ሠላምታ አቀረቡ፡፡

ይህ የኦሮሞ ሽማግሌዎች ስብሰባና አጠቃላይ ሂደት ቄስ ኢተፋ ጉበና አምባሳደር ብርሃኑ ዲንቃና አቶ አበራ ቶላ ባቀረቡት ሀሳብ መሠረት መሆኑን አስረዱ፡፡ ይህም ጥቅምት 22 - 23/2001 በኢምፔሪያል ሆቴል 147 የሚሆኑ ከኦሮሚያ የተወጣጡ የኦሮሞ ሽማግሌዎች የተነጋገሩትን ሃሳብ በእንግሊዘኛና በአፋን ኦሮሞ የተፃፈውን ለጠቅላይ ሚንስትሩ አቀረቡ፡፡ ከዚያም ተጨማሪ ማብራራዎች ታከለውበት ጠቅላይ ሚንስተሩም በዚያ ዙሪያ ሃሳባቸውን ሰጡ፡፡

አቶ መለስ እንዳሉት የሽግግር መንግሥቱን ቻርተር ከኦነግ ጋር ሆነው ማለትም ኦነግ ራሱ በተሳተፈበት የተቀረፀ መሆኑን ገለፁ፡፡

ባሁኑ ወቅት በኦነግና በመንግሥታቸው መካከል ችግሮች የሉም ማለት ባይቻልም፣ ያለ ዲሞክራሲም ለጋ ቢሆንም ያለን ሥርዓት ግን ጤናማ እንደሆነው ገለፁ፡፡ ይህም ዲሞክራሲ በዚህ ጤናማ ሥርዓት ውስጥ ሊያድግ እንደሚችል እምነታቸውን ገለፁ፡፡

በእሳቸው እምነት ኦነግ ችግሮችን በጦርነት ለመፍታት መግፋት የለበትም ምክንያቱም ለጦርነት በቂ ምክንያት የለም ብለው አስረዱ፡፡

ያም ሆኖ ከኦነግ መሪዎች ጋር ለመደራደር ጥረት ያላደረግንበት ጊዜ የለም ካሉ በኋላ በተለይ ከምርጫ 97 ወዲህ እኔ በግሌ ከአቶ ሌንጮ ለታ ጋር ሁለት ጊዜ በአካል ተገናኝተን ተነጋግርን በደብዳቤም ሲንፃፃፍ ነበር ብለዋል፡፡

ሂደቱ በእንዲህ እንዳለ ጊዜው ከቅንጅት ጋር ግጭት ውስጥ በነበርነበት ወቅት ስለነበረ አንዳንድ ከእውነቱ የራቁ አሉባልታዎች ተነሱ፡፡ ይህም አሁን መንግሥት ከኦነግ ጋር

ሊደራደር የፈለገው ቅንጅት መፈናፈኛ ስላሳጠው ነው በማለት ጥረቱ እንዲከሽፍ አደረጉ:: በኦነግ በኩልም ነገሩን ለመቀጠል ፍላጐት አልታየም ነበርና ይህም በውስጡ ካለው የተለያዩ አመለካከቶች ነው፤ አሁንም ቢሆን ለጦሪነት በቂ ምክንያት በለሌበት ሁኔታ ኦነግ አቋሙን እንዲህ መግፋት የለበትም ብዬ አምናለሁ ብለዋል ጠቅላይ ሚንስትሩ::

በቅንጅትና በእኛ መካከል የተፈጠረው ግጭት ዋጋ አስከፍሎን ነገሩ በእርቅ ተጠናቆአል:: ይህ የቅንጅት ጉዳይ በሠላም የተፈታው የአቋም ልዩነት ባለበት ሁኔታ ነው:: ይህ ከሆነ በአቋም ልዩነት ከኦነግ ጋር በሠላም ግጭቶችን ለመፍታት የሚያስቸግረን ነገር ይኖራል ብዬ አላምንም:: እንዲያውም አሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከኦነግ ጋር ካለን የሀሳብ ልዩነት ይልቅ ከቅንጅት ጋር ያለን ይሰፋል ብለዋል::

ስለዚህ ነው ይህ ጉዳይ በዕርቅ ማለቅ አለበት ብለው ሽማግሌዎቹ ያቀረቡልኝን የተቀበልኩት አሉ አቶ መለስ::

ያም ሆኖ ግን አሁን የጀመራችሁት የዕርቅ ሂደት የአስፋልት መንገድ እንደማይሆንላችሁ እርግጠኛ ነኝ፤ ምክንያቱም አሉ አቶ መለስ ካሉኝ ሁለት ስጋቶች አኳያ እነርሱም:-

1. የውጭ ጣልቃ ገቢነት በተለይም የኤርትራ መንግሥት ይህንን ዕርቅ ስለማይፈልግና እንዲያውም ባሁኑ ወቅት የኦነግ መሪዎችን ፓስፖርት ቀምቶአቸው የቁም እሥረኛ አርጉአቸው ስላለ እነዚህ ሰዎች ከዚህ እንደት ተላቅቀው መደራደር እንደሚችሉ አንደኛው ስጋቴ ነው ካሉ በኋላ
2. ሁለተኛው ስጋቴ ደግሞ በኦነግ ውስጥ ያለው የሀሳብ ልዩነት ወይም የተለያዩ ሀሳቦች መሆናቸውን አስረድተው ቢሆንም ሽማግሌዎቹ የሚቻላቸውን እንዲጥሩ አሳስበዋል:: እኛም ደግሞ እንደመንግሥት ጥረታችሁን እንደግፋለን ብለዋል::

ይህንን ሁሉ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እነ ቄስ ኢተፋ የኦሮሞ ሽማግሌዎችን እናማክራለን ብለው ሲጠይቁኝ ፈቀድኩላቸው:: ከዚህም ጋር በተያያዘ የኦሮሞ ሽማግሌዎቹ ከእኔ ጋር እንዲገናኙ መድረክ ይዘጋጅ ሲባል ጉዳዩን ተቀብለን በዚሁ እንዲቀጥል ፈቀድን ብለው ሃሳባቸውን አጠናቀቁ::

በመቀጠልም የኦሮሞ ሽማግሌዎች ከ21/2/2001 በእምፔሪያል ሆቴል ተሰባስበው ለመንግሥት ለኦነግና መሪዎች ያስተላለፉትን የሠላምና የእርቅ ጥሪ በኦሮምኛ

የተዘጋጀውን የአባገዳው መሪ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አስረከቡ፡፡ በእ ንግሊዘኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን ደግሞ ፕሮፌሰር እንዳሻው አንድ ኮፒ ለአቶ መለስ ሰጥተው በእጃቸው ከቀረው ደግሞ በንባብ አሰሙ፡፡

በዚያም ላይ በማከል አምስት የኦሮሞ ሽማግሌዎች ተጨማሪ ሀሳቦች አነሱ፡፡ ከእነዚህም ሽማግሌ ውስጥ ከኬንያና ከሚኖሶታ የመጡ ሁለት ሰዎች ናቸው፡፡ ወ/ሮ ዱሬ ነጋሣ ከኬንያና አቶ መሀመድ ከሚኖሶተ በመጨረሻ ከመዝሙረ ዳዊት 28:8 ላይ ወ/ሮ ዱሬ ነጋሣ ያለውን በማንበብ ያላቸውን ሀሳብ አጠናቀቁ፡፡

እነዚህም ሽማግሌዎች ካነሱአቸው ነጥቦች አንዳንዶቹ:-

1. አለመግባባቱ በዕድገታችን ላይ የራሱ አሉታዊ እንድምታ እንዳለው
2. ምሁራን አገር ለቀው እየወጡ መሆናቸውን
3. በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ኦሮሞዎች ከውጭ ወደአገር ውስጥ ገብተው እንቬስት ለማድረግ ፍራቻ እንዳለባቸው
4. በኦሮሚያ ውስጥ ከፍተኛ ችግር መኖር /ከሥራተኛ ቅጥር ጀምሮ መባረር
5. የኦሮሞ ሕዝብ ሀሳቡን በነፃ ለመግለፅ አለመቻል
6. ኩርፍያና ወዘተ በማካተት ሽማጌሌዎቹ ያላቸውን ሃሳብ በስፋት አቅርበዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቃልና በጽሑፍ የተነሱትን ሀሳቦችን ካዳመጡ በኋላ እንደሚከተለው ብለዋል፡፡

1. መንግሥት ከኦነግ ጋር ጦርነት ለመግጠም በቂ ምክንያት የለውም፤ በዚህም ጦርነት አምነንበትም አናውቅም፡፡ ጦርነት እንደ ጀብዱነት መቆጠር የለበትም፡፡ መራገጥ ከሆነ እንኳንስ ሰው አህያም ይራገጣል፡፡ ሰውን ግን ልዩ የሚያረገው ቢኖር ማሰብ መቻሉ ነው፡፡ ከመንግሥቱ ሃይለማርያም ጋር የተደረገው ጦርነት በቂ ምክንያት ነበረው፡፡

2. ከኦነግ ጋር ያለው ጉዳይ በሰላም ካልተፈታ በልማታችንና እድገታችን ላይ የራሱ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው እውን ነው፡፡ በሰላም ይፈታ ብለን ሲንል ኦነጐች እኛ

የምንወደውን ይወደዱ እኛ የምንጠላውን ይጥሉ ማለታችን እንዳልሆነ መታወቅ አለበት የሀሳብ ልዩነትን እንደ ልዩነት ተቀብለን የመቻቻል ልማድን እናዳብር ማለታችን ነው::

3. ኦነግ በሰላማዊ መንገድ ገብቶ ተደራድሮ ችግሮቻቸውን መፍታት አለባቸው:: ይህ ያለንበት ዘመን ነገሮችን በጦርነት የሚፈታበት መንገድ ሳይሆን የሚወያዩበትና የሚደራደሩበት ወቅት ነው፤ ከዚህ ውጭ ሌላ አማራጭ ተጠቅመው ሽብር ለመፍጠር የሚመርጡ ከሆነ እንደ መንግስት ሰላምና ፀጥታን ለማስጠበቅ ግዴታ አለብን:: በአዲስ አበባ ታክሲዎች ላይ ፈንጂ በማጥመድ ሰላማዊ ሰዎችን በማጥቃት የሚመጣ ነገር የለም:: ይህንንም የሚያደርገው ለገሠ ወጊ የሚባል ሰው መሆኑን በግሌ ደርሽበታለሁ ብለዋል::

4. ለእኛ የኦነግ ሰዎችን በአካልም ይሁን በአዕምሮ በማሰር የሚገኘው እርካታ የለንም ብለዋል:: ዳሩ ግን ክብሪት ይዞ ሲመጣብን የሚናደርገው ነገር ይህ ነው አሉ:: ያም ሆኖ ግን ንግግር ይቁም ጦርነት ይቀጥል የሚል እምነት የለንም:: ጦርነት እስኪያበቃ ድረስ ውይይት አይቀርም::

5. አሁን የተጀመረው የሽምግልና ሥራ ከመቼውም ጊዜ በላይ ስኬታማ ይሆናል የሚል ፅኑ እምነት አለኝ ብለዋል:: ስለዚህ ይህንን ሂደት ከልብ እደግፋለሁ ብለዋል::

በመጨረሻም:-

1. ልዩነቱ በሠላም እንዲፈታ ከልብ እንደግፋለን እናምንበታለንም ያለው ትልቅነት ከጡንቻ ሳይሆን ከጭንቅላት ነው::

2. የተፈለገው ሰላም እስኪመጣ ድረስ ከሰላም ማስጠበቁ ጐን ለጐን ጥረታችንን እንቀጥላለን ጦርነት የምኒደግፍ አይደለንም፤ በተባራሪ ጥይት ቤቶች ይቃጠላሉ፤ ሕይወት ይጠፋል:: ስለዚህ ነገሩ በሠላም እንዲፈታ እኛም ከእናንተ ጋር እንሠራለን::

3. እንኳንስ ኦነግ ሞአ አንበሳም መብት አለው፤- ዓላማውን በሰላማዊ መንገድ ለማራመድ ካሉ በኋላ ለሽማግሌዎቹ በንግግራችሁ ውስጥ አንድ ነገር ብልጭ ብሎብኛል ይሄውም እኛ የኦነግ አባላት ወይም ደጋፊዎች አይደለንም ስትሉ

ነው፤ ብትሆኑስ እኛ እንደልዩነት እንጂ እንደጠላት አንቆጥርምና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ስላለ ከዚሁ አንፃር መታየት አለበት ብለዋል።

6. ቀጥለውም ሽማግሌዎቹ በዚህ ዕርቅ ውስጥ በኦነግ ጉዳይ ላይ በመሳተፋችን ምን ዋስትና አለን ብለው ላነሱት ጥያቄ ሲመልሱ፡- አንደኛ ዋስትናሁ እግዚአብሔር ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ሕግና ሥርዓቱ ነውና ስለዚህ ስጋት እንዳያድርባችሁ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ ብለዋል።

በመጨረሻም ይህንን ጉዳይ ይዘው ይሰሩበት ለነበሩትና ላሉት ለቄስ ኢተፋ፣ ለአምባሳደር ብርሃኑ ድንቃና ለአቶ አበራ ቶላ ምሥጋናቸውን አቅርበው ጥረቱ እንደሚሳካም ያላቸውን እምነት ገለፁ። አክለውም ይህ የኦሮሞ ሽማግሌዎች ከኦነግ በላይ አቅም እንዳለውና ነገሮችን መለወጥ እንደሚችል ገለፁ።

በመጨረሻም ቄስ ኢተፋ ጉበናና አምባሳደር ብርሃኑ ዲንቃ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ካላቸው ውድ ጊዜ መስዋዕት አድርገው በጽ/ቤታቸውን ስላነጋገሩን ከልብ ምሥጋናቸውን አቀረቡ። ውይይቱም 6:01 ሰዓት ላይ አበቃ

ይህ ማስታወሻ የተያዘው ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ 33ቱን የኦሮሞ ሽማግሌዎችን በቤተ መንግሥት ተቀብሎአቸው ስለ ኦሮሞ ነፃነት ግንባር ባነጋገሩበት ወቅት አብሬአቸው በቦታው በመገኘት የተከታተልኩትን የግሌ ልዩ ማስታወሻ ነው።

ይህም ጥቅምት 24 ቀን 2001 ዓ/ም ነው።

## *አጠቃላይ የግል ግምገማ*

1. የኦሮሞ ሽማግሌዎቹ ይህንን የሰላም ወይይት ከግብ ለማድረስ ልባዊ መነሳሳትና በራስ የመተማመን ስሜት ነበራቸው

2. ጠቅላይ ሚ/ሩ ከመቼው ጊዜ በላይ ከኦነግ ጋር ለመደራደር የቆረጡና የወሰኑ እንደሆነ ይነበብባቸዋል።

3. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያነሱአቸውን ሁለቱን ስጋቶች ማለትም የውጭ ሃይላት ጣልቃ ገቢነትና በኦነግ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሀሳቦች እኔም

የሚጋራ ሲሆን በውጭ አገራትም ያሉ የኦሮሞ ሽማግሌዎች በዚህ ጉዳይ ላይ እንደምሰሩ መስራት እንደሚጠበቅባቸው ይታየኛል፡፡

4. ይህ የሽማግሌዎች ቡድን ከውጭ መንግሥታት በላይ ተሰሚነት ስላለው በዚህም ስለሚንቀሳቀስ የኦሮሞ ሕዝብ ድጋፍ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

5. ኦህዴድ የኦሮሞ ፖለቲካ ድርጅት መሆኑና ኦነግም በሠላም መሥራት ከቻለ ሁለቱ የፖለቲካ ድርጅቶች በሕዝቡ መካከል መኖራቸው ለኦሮሞ ሕዝብ እንደ ጥቅም እንጂ እንደ ጉዳት አይቆጠርም ምክንያቱም ሕዝቡ አማራጭ ይኖረዋልና የሚል እምነት አለኝ፡፡

ፈቃዱ ቤኛ (አቶ)

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ከሽማሌዎች አንዱ